# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት

## International Ethiopian Women's Organization

**IEWO,** ***P.O. Box 56729, Washington DC, 20040 , USA***

---

***" ሀገርን ከአደጋ ለማዳን፤ ህልውናዋን ለመጠበቅና አልፎም ሁለገብ ዕድገቷን ለማረጋገጥ ሴቶች በህብረተሰቡና በሀገሪቷ የሚኖራቸው መብት፥ እኩልነትና ነፃ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ የሴቶች መብት የማይከበርብት ሀገር ከዴሞክራሲ የተጣላ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሴቶች ተገቢ ቦታቸውን በህብረተሰቡ ከአረጋጋጡ ለሀገር ዕደገትና ብልፅግና ዋስትና ይገኛል፡፡ ስለዚህም ሴቶች በራሳቸው ተደራጅተው ለመብታቸው መታገላቸው አስፈላጊና ወሳኝ በመሆኑ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ተመስርቷል፡፡" ዓኢሴድ***

## ለኢትዮጵያውያን በሙሉ

## <u>የሰብስባ ጥሪ</u>

***ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ሴቶች ለመብታቸው ለመታገል መደራጀት እንዳለባቸው በመገንዘብ በመላ ዓለም ተሰራጭተው የሚገኙትን የኢትዮጵያ ሴቶችን ለማደራጀት የተመሰረተ ነው፡፡ ለሴቶች ዕድገትና ጤንነት፤ለሰላም፤ፍትህና እኩልነት ብሎም በሀገራቸው ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ የሚያስችል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የተመሰረተ ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ ሴቶች በሀገራቸው ውስጥ በሁሉም መስክ (በትምህርት፤ በሙያ፥ በፖለቲካ ወዘተ ) መብታቸው እንዲከበርና እንዲረጋገጥ ለማድረግ የሚጥር ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ነው፡፡***

***ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት የመጀመሪያ ጉባዔውን የሚያካሂደው በሀገራችን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ይዞ ያለውን የአድዋ በዓልንና በተለይም የአድዋ ድል ባለቤት የሆኑትን እቴጌ ጣይቱን በማስታወስ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ታሪካዊ ወቅት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉ አርበኞችን፥ ለሀገር ህልውናና ለወገን ደህንነት በየጊዜው ተጋድሎ ያደረጉና በማድረግ ላይ ያሉ ሴቶችን የምንዘክርበት ይሆናል፡፡ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ የሴቶች ድርጅት የመጀመሪያ ጉባዔውን የሚያካሂደው በመላው ዓለም ለሰው ልጆች ደህንነት የታገሉና የሚታገሉ እህቶቻችን የሚያከብሩትን የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን በጣምራ በማክበር ይሆናል፡፡***

***ስለዚህም ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት የመጀመሪያ ጉባዔውን ከማድረጉ በፊት በሚካሄደው የመክፈቻ በዓል ላይ እንዲገኙ በአክብሮት ተጋብዘዋል፡፡***

**የስብስባ ቀን**____March_3/2007   1:00 pm - 6:00 pm
**የስብሰባ ቦታ**__  Unification Church
 1610 Columbia rd.  (16th and Columbia) Washington DC NW

***አዘጋጅ ኮሚቴ***

***ዓ ኢ ሴ ድ***